ARCH
Disability Law Centre

425 Bloor Street East, Suite 110
Toronto, Ontario   M4W 3R5
www.archdisabilitylaw.ca

(416) 482-8255 (Main) 1 (866) 482-ARCH (2724) (Toll Free)
(416) 482-1254 (TTY)   1 (866) 482-ARCT (2728) (Toll Free)
(416) 482-2981 (FAX)  1 (866) 881-ARCF (2723) (Toll Free)

2008/07

# መድልዎ እና የአይምሮእና ድጋፎችን የሚጠቀሙ ሰዎች ጤንነት አገልግሎቶችን

ይህ የእውነታ ዝርዝር አንተን እንዲረዳ የታለመው የአይምሮ ጤንነት አገልግሎቶች እና እርዳታዎችን የምትጠቀም ወይንም ከዚህ በፊት ተጠቅመህም ከሆነ፤ ከቤተሰብ ዶክተር፡ ነርስ፡ ሳይካትሪስት፡ ሳይኮሎጂስት ወይም ከተመሳሳይ ሰዎች። በተጨማሪም አንተን ይጠቅማል ይህ ከሆነ፡

- ከአንተ የአይምሮ ጤንነት በተያያዘ አመል ምክንያት ሬስቶራንት ወይም ሌላ የንግድ ማእከል ለቀህ እንድትወጣ ተጠይቀሃል፤
- በአይምሮ ጤንነት ታሪክህ የተነሳ ለስራ አልተቀጠርክም አልያም የስራ አለቃ እድገት አልሰጠህም በአይምሮ ጤንነትህ ታሪክ ምክንያት፤
- በሳይካትሪ አካለ ስንኩልነትህ ምክንያት የስራ ባልደረቦችህ ስራ ላይ አስጨንቀውሃል፤
- ቤት አከራይ በአንተ የአይምሮ ጤንነት ታሪክ የተነሳ ላንተ ቤት አላከራይም ብሏል፤
- መንግስት -የፌዴራል መንግስትን ፡ ክፍለ ሀገር ወይም አንተ የመትኖርበትን ከተማ አጠቃሎ- በሳይካትሪ አካለ ስንኩልነትህ ምክንያት እየበደለህ ነው።
- አንድ ህግ ወይም የመንግስት ፖሊሲ በሳይካትሪ አካለ ስንኩልነትህ ምክንያት እየበደለህ ነው።
- በአሁኑ ወቅት ችግር ባይኖርብህም ወይም ምልክቶቹ ባይታዩብህም አንድ ሰው የአይምሮ ጤንነት ጉዳይ አለህ ብሎ በማሰቡ መክንያት በደል ፈጽሞብሃል፤ ወይም
- ማንኛውም ሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች።

**በአይምሮ ጤንነት ጉዳይ መያዝ አንድ የአካለ ስንኩልነት አይነት መሆኑን እና ማንኛውም አይነት የአካል ስንኩልነት ካላቸው ሰዎች በተመሳሳይ አንድ አይነት መብቶች እንዳሉህ በጣም ማወቅ ያስፈልጋል ።**

**መድልዎ እና ጭንቀት ሊፈጸምብህ አይገባም በአይምሮ ጤንነትህ ጉዳዮች ምክንያት።**

**መድልዎ እና ጭንቀት ሊፈጸምብህ አይገባም፡ አሁን ወይም ባንድ ወቅት በሳይካትሪ ግቢ ወይም ሆስፒታል ውስጥ ታካሚ ስለነበርክ።**

እዚህ ላይ ያሉት አብዛኛዎቹ መረጃዎች ኦንታርዮ ለሚኖሩ ሰዎች ጠቃሚ ናቸው።

## መድልዎ ማለት ምንድነው?

ይህ የእውነታ ዝርዝር ያንተን የሰባዊ መብቶች የተመለከተ ነው። መብቶችህን ማወቅ እራስህን እና ሌሎችን ከመድልዎ እና ከአበሳ እንድትከላከል ይረዳሃል።

መድልዎ ማለት ያለበቂ ምክንያት መበደል ወይም መለየት ነው፤ ለምሳሌ በዘር፡ ጾታ፡ የጋብቻ ሁኔታ፡ የትውልድ ቦታ፡ እድሜ ወይም አካል ስንኩልነት ምክንያት። አንድ ሰው አንተን ከበደለህ፡ ወይም ለምሳሌ በአካል ስንኩልነትህ አልያም በዘርህ ምክንያት እንደሌሎች ሰዎች ላንተ ተመሳሳይ እድል ካልተሰጠህ መድልዎ ደርሶብሃል ማለት ነው።
ለምሳሌ በዘርህ ወይም የአካለ ስንኩልነትህ ምክንያት የስራ አለቃህ ከስራ ካባረረህ አለቃህ አንተ ላይ መድልዎ ፈጽሟል ማለት ነው።

በተጨማሪም ማስጨነቅ የመድልዎ አይነት ነው። እሱም የሚያጠቃልለው፡ አንተን ዝቅ የሚያደርጉ ወይም የሚያስቀይሙ እርምጃዎችን፡ ትችቶች ወይም ስድቦችን ነው። እነኚህ ትችቶች በዘርህ፡ ጾታ፡ ዜግነት፡ ሃይማኖት፡ የአካል ስንኩልነት ወይም በሌላ የማንነትህ ክፍሎች ላይ የተመረኮዙ ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም ማስጨነቅ የሚከሰተው አንድ ሰው አንተ የማትቀበለውና የማይመችህ ነገር መሆኑን እያወቁ ሲሉህ ነው። የማስጨነቅ ምሳሌዎች ናቸው አንድ ሰው፡

- ዘረኛ ቃላት ወይም ቀልዶች ሲል፤
- በሳይካትሪ አካል ስንኩልነትህ ምክንያት ሲሰድብህ፤
- የአንድ የዘር ወይም ሃይማኖት አባሎችን የሚያዋርዱ ካርቱኖች ወይም ፎቶዎችን ማሳየት፤ ወይም
- ባንተ ዘር፡ ቀለምወይም አካለ ስንኩልነት ምክንያት ስሞች ሲሰጥህ።

## <u>የኦንታርዮ የሰባዊ መብቶች ህግ</u>

*የኦንታርዮ የሰባዊ መብቶች ህግ* ክፍለ ሃገራዊ ህግ ነው። የሚደነግገውም ኦንታርዮ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው ያለምንም መድልዎ እኩል መብቶችና እድሎች እንዲኖረው ነው። ህጉ አንተ ላይ በዘርህ፡ ቀለም፡ ጾታ፡ አካለ ስንኩልነት ወዘተ ምከንያት ከሚደርሰው መድልዎ እና ጭንቀት እንደሚጠብቅህ ይገመታል። "አካለ ስንኩልነት" የሚያጠቃልለው የአይምሮ አካለ ስንኩልነትን እና አብዛኛዎቹን የአይምሮ ጤንነት አገልግሎቶች እና ድጋፎች የሚጠቀሙ ሰዎችን ነው።

ከመድልዎ እና ጭንቀት ነጻ የመሆን መብት አለህ፤ በሱቆች፡ ሬስቱራንቶች፡ ትራንዚት፡ ሆስፒታሎች፡ ትምህርት ቤቶች፡ ኢንሹራንስ፡ የቤት አገልግሎት፡ ኮንትራቶች፡ በስራ፡ እና የሰራተኞች ማህበሮች አባልነት ውስጥ። ለምሳሌ፤

- የአካል ስንኩልነቶች ያላቸው ሰራተኞች አካለ ስንኩልነቶች ከሌላቸው ሰዎች ጋር አንድ አይነት እድሎች እና ጥቅሞች አላቸው። አንዳንድ ጊዜ የአካል ስንኩልነቶች ያላቸው ሰራተኞች የስራ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ አሰሪዎቻቸው የስራ ቦታ ለውጦች እንዲያደርጉላቸው ይፈልጉ ይሆናል።
- በተጨማሪም የአካል ስንኩልነቶች ያላችው ደንበኞች በእኩል የመስተናገድ እና እኩል ቀረቤታ የማግኘት መብት አላቸው፤ በሬስቱራንቶች፡ ሱቆች፡ ሆቴሎች፡ እና የፊልም ቤቶች፡ የአፓርታማ ህንጻዎች፡ ትራንዚት እና ሌሎች የህዝብ ቦታዎች ውስጥ። ትምህርት ቤቶችም የአካል ስንኩልነቶች ላላቸው ተማሪዎች ምቹ እንደሆኑ ማረጋገጥ አለባቸው።
- የቤት አከራዮች በአንተ ዘር፡ ጾታ፡ እድሜ፡ ቀለም፡ አካለ ስንኩልነት፡ ወዘተ ምክንያት ቤት አናከራይህም ማለት አይችሉም። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ስለመኖርያ የእኩል መብቶች ማእከልን በ (416-944-0087) ላይ መደወል ትችላለህ።

*በህጉ ስር ስላሉት መብቶችህ እና ግዴታዎችህ አስመልክቶ ጥያቄዎች ካለህ ነጻ የህግ መረጃ እና ምክር ለማግኘት ARCHን መጠየቅ ትችላለህ።*

አንድ አለቃ፡ የቤት አከራይ፡ ወይም የአገልግሎት ሰጪ በአንተ የአይምሮ ጤንነት አካለ ስንኩልነት ምክንያት አንተን ከለየ እና ግፍ ካደረሰብህ ለኦንታርዮ የሰባዊ መብቶች ጉባኤ ማመልከቻ ማስገባት ትችላለህ። ለጉባኤው የሚገባው ማመልከቻ በደሉ ከደረሰብህ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት። ነገር ግን ከአንድ አመት በኋላም ማመልከት ይቻል ይሆናል። እንዴት የሰባዊ መብቶች ማመልከቻ እንደምታስገባ የበለጠ መረጃ እና ዝርዝር ለማግኘት እባክህ ከጉባኤው ጋር ተገናኝ፡

Human Rights Tribunal of Ontario
655 Bay Street, 14th Floor
Toronto, ON M7A 2A3

ለአካባቢው የስልክ ጥያቄ፡ (416) 326-1312
በነጻ ስልክ ለመጠየቅ፡ 1-866-598-0322
TTY (የአካባቢው) ፡ (416) 326-2027
TTY (በነፃ)፡ 1-866-607-1240
ፅህረ ገጽ: www.hrto.ca

የሰባዊ መብቶች የህግ ድጋፍ ማእከል ለሰዎች የግል የሆነ የህግ ምክር ሊሰጥ ይችላል ማመልከቻ ማስገባትን አስመልክቶ። ማመልከቻ ከገባም በኋላ የህግ ምክር እና ውክልናን ሊሰጥ ይችላል ። ስለ የሰባዊ መብቶች የህግ ድጋፍ ማእከል አገልግሎቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክህ ከማእከሉ ጋር ተገናኝ፡

Human Rights Legal Support Center
400 University Avenue, 7th Floor
Toronto, ON

ለአካባቢው የስልክ ጥያቄ፡ (416) 314-6266
በነፃ ስልክ ለመጠየቅ፡ 1=866-625-5179
TTY፡ (416) 314-6651
TTY(በነፃ)፡ 1-866-612-8627
ፅህረ ገጽ www.hrlsc.on.ca

## የካናዳ የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ

*የካናዳ የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ የፌዴራል አሰሪዎች ወይም የአገልግሎት ሰጪዎች፤ እንደ ባንኮች፡ የአየር መንገዶች፡ የቴሌቪዥን እና የራድዮ ጣቢያዎች፡ የቴሌፎን ኩባንያዎች፡ የባቡር መንገዶች እና የማእድን አውጪዎች የሚያደርጉትን መድልዎ ያስቀማል ተብሎ ይጠበቃል።*

አንድ የፌደራል አሰሪ ወይም የአገልግሎት ሰጪ በአንተ ዘር፡ ቀለም፡ ጾታ፡ አካለ ስንኩልነት፡ እድሜ እና ወዘተ ምክንያት አንተ ላይ መድልዎ ወይም ጭንቀት እንዳያደርስ ህጉ ይደነግጋል።
"አካለ ስንኩልነት" የሚያጠቃልለው የአይምሮ አካለ ስንኩልነትን እና የአይምሮ ጤንነት አገልግሎቶች እና ድጋፎች የሚጠቀሙ ሰዎችን ነው።

በአንድ አመት ውስጥ ለካናዳ የሰባዊ መብቶች ኮሚሽን የሰባዊ መብቶች አቤቱታ ማስገባት ትችላልህ። አቤቱታ ለማስገባት በስልክ፡ ፋክስ ወይም በደብዳቤ ከኮሚሽኑ ጋር ተገናኝ።


Canadian Human Rights Commission
344 Slater Street, 8th Floor
Ottawa, Ontario K1A 1E1
ስልክ፡ (613) 995-1151
በነፃ፡ 1-888-214-1090
TTY ፡ 1-888-643-3304
ፋክስ፡ (613) 996-9661
ዕህረ ገጽ: http://www.chrc-ccdp.ca/


ለካናዳ የሰባዊ መብቶች ኮሚሽን የምታስገባው አቤቱታ የፌደራል አሰሪን ወይም የአገልግሎት ሰጪን ብቻ በመቃወም ነው። ሱቅ፡ ሬስቱራንት፡ ሆቴል፡ ሆስፒታል፡ የጤና አገልግሎት ሰጪ፡ ትምህርት ቤት፡ ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲን በመቃወም አቤቱታ ማስገባት ክፈለክ አቤቱታህን ማቅረብ ያለብህ አንተ ያለህበት ክፍለ ሀገር ላለው የሰባዊ መብቶች ኮሚሽን ነው። ክፍለ ሀገሮቹ እና ግዛቶቹ ተመሳሳይ ፀረ መድልዎ ህጎች አላቸው።

## <u>የመብቶች እና ነጻነቶች ቻርተር</u>

*በመብቶች እና ነጻነቶች ቻርተር* ስር የሚጠበቁ አንዳንድ መብቶች አሉህ። ቻርተሩ የህገመንግስቱ አካል ነው፤ እሱም "የካናዳ የበላይ ህግ" ነው። *ቻርተሩም* በህጎችና በመንግስት እርምጃዎች ከሚፈፀም መድልዎ ሰዎችን ይጠብቃል። ለሁሉም ሰው አንድ አይነት ጥቅሞች እና በህግ ስር አንድ አይነት ጥበቃዎችን ይሰጣል፤ በዘርህ፡ እድሜ፡ ጾታ፡ የአካል ስንኩልነት እና ወዘተ ምክንያት መድልዎ እንዳይኖር። "የአካል ስንኩልነት" የሚያጠቃልለው የአይምሮ ጤንነት ጉዳዮችን ነው።

መንግስታት ህጎችን በሚያወጡበት ወቅት *ቻርተሩን* ያከብራሉ። ፍርድ ቤቶችም ጉዳዮችን ሲያዩ *ቻርተሩን* ግምት ወስጥ ማስገባት አለባቸው። አንድ ህግ ወይም የመንግስት እርምጃ *ቻርተሩን* የሚጥስ ከሆነ እነዛ ህጎች እንዲሻሩ ፍርድ ቤትን መጠየቅ እንችላለን።

*ቻርተሩ* የሚመለከተው ህጎችን እና የመንግስት እርምጃዎችን ብቻ ነው። አንድ የግል የንግድ ድርጅት አንተ ላይ መድልዎ ከፈጸመ ለክፍለ ሀገርህ ወይም የግዛትህ የሰባዊ መብቶች ኮሚሽን መደወል አለብህ።

መድልዎ እንደደረሰብህ ለማረጋገጥ ይህን ማሳየት አለብህ፤

- ከሌሎች በተለየ ታይተሃል
- ለአንተ የተሰጠው ልዩ አስተያየት በዘርህ፡ ሃይማኖት፡ ጾታ፡ እድሜ፡ የአካል ስንኩልነት እና ወዘተ መክንያት ነው።
- ልዩ አስተያየቱ ሰውየው ከሌሎች ሰዎች ጋር አንድ አይነት አክብሮት እንደማይገባው እንዲመስል ያደርጋል።

መድልዎ እንደደረሰብህ ማረጋገጥ ባትችልም እንኳን ህጉ በ*ቻርተሩ* ስር ይጸናል አስተያየቱ "ነጻ በሆነ ዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ውስጥ ትክክል እና የሚገባ" ከሆነ።

አንድ ህግ ወይም መንግስት የቻርተር መብቶችህን አያከብርም ብለህ የምታሥብ ከሆነ መንግስቱን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ትችላለህ። ይህ ትልቅ እርምጃ ነው። ፍርድ ቤት ከመሄድህ በፊት ስለ ጥቅሞቹ እና ስለሚከተሉ ውጤቶች በሚገባ ማሰብ ያስፈልግሃል። ለምሳሌ ህጋዊ ወጪዎች በጣም ውድ ሊሆኑ ይችላሉ። ረጅም ጊዜም ሊወስድ ይችላል። ስለነገሩ ፍላጎት ካላቸው ከሌሎች ሰዎች ጋር መስራት ትፈልግ ይሆናል። የARCH የአካለ ስንኩልነት ማእከልን አጠቃሎ ብዙ የተለያዩ ድርጅቶች በቻርተሩ ተቃውሞዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

## ሌሎች አጠባበቆች

አንዳንድ የስራ ቦታዎች ፀረ ወድልዎ ፖሊሲዎች አላቸው። የሰራተኝ ማህበር አባል ከሆንክ፡ ለበለጠ መረጃ ከማህበሩ ሃላፊ ጋር መገናኘት ትችላለህ። አንዳንድ ሆስፒታሎች ስለመድልዎ ፖሊሲዎች አላቸው። ሆስፒታልህ ውስጥ ስላሉት ደንቦች የበለጠ መረጃ ለማግኘት የህመምተኛ ተወካዮችን ወይም የሆስፒታሉን ክፍል ሰራተኞች ጠይቅ።

በተጨማሪም ስለ ሰባዊ መብቶችህ **ከማህበረሰብ የህግ ኬላ** ምክር ማግኘት ትችላለህ። የማህበረሰብ የህግ ኬላዎች ገቢያቸው አነስተኛ ለሆኑ ሰዎች እና ማህበረሰቦች የህግ አገልግሎቶች ይሰጣሉ። በአንተ አቅራቢያ ያለውን የማህበረሰብ የህግ ኬላ ለማግኘት 416-979-1446 ላይ ደውል። በተጨማሪም በዮርክ ዩንቨርስቲ የሚገኘው **የማህበረሰብ ህጋዊ እርዳታ አገልግሎት ፕሮግራም** (CLASP) የአይምሮ ጤንነት ጉዳዮች ላላቸው ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል። እነሱን በ 416-736-5029 ላይ ማግኘት ትችላለህ።

የፍርድ ቤት ጉዳይ ከመጀመርህ በፊት ከጠበቃ ጋር መነጋገር ያስፈልግሃል። የጊዜ ገደቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህም ማለት አንተ ላይ መድልዎ ከተፈፀመ በኋላ ቶሎ የፍርድ ቤት ጉዳይ መጀመር አለብህ። የኦንታርዮ ጠበቃ ለመቅጠር ከፈለክ በላይኛው ካናዳ የህግ ማህበረሰብ ለሚንቀሳቀሰው **የጠበቃ ፈላጊ አገልግሎት** መደወል ትችላለህ። የጠበቃ ፈላጊ አገልግሎቱ በመድልዎ እና የሰባዊ መብቶች ላይ የሚያተኩር የጠበቃ ስም ይሰጣል። በተጨማሪም ለግማሽ ሰአት ነፃ ምክር ይሰጣል። የአገልግሎቱ የስልክ ቁጥር 1-800-268-8326 ወይም 416-947-3330።

## ስለ አርች

ARCH የአካለ ስንኩልነት የህግ ማእከል ልዩ የህግ ድጋፍ እርዳታ ማእከል ሆኖ የአካል ስንኩልነት ያላቸው ሰዎች፡ የአይምሮ ጤንነት ጉዳዮች ያላቸውን ሰዎች አጠቃሎ የእኩልነት መብታቸውን ለማስጠበቅ እና ለማራመድ የተመሰረተ ነው።

ARCH ስለ መድልዎ መረጃ አጠቃሎ ነፃ፡ ምስጢራዊ፡ እና መሰረታዊ የህግ መረጃ የአካል ስንኩልነቶች ላላቸው ሰዎች ይሰጣል ። ኣርች ይህንን አገልግሎት የሚሰጠው በስልክ ነው። ከአካል ስንኩልነትህ የተነሳ በስልክ ከእኛ ጋር መነጋገር ካልቻልክ ያንተን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ካንተ ጋር ለመግባባት እንሞክራለን።

425 Bloor Street East, Suite 110
Toronto, Ontario, M4W 3R5
ስልክ 416-482-8255
በነፃ 1-866-482-2724
TTY 416-482-1254
በነፃ 1-866-482-2728
ፋክስ 416-482-2981
በነፃ 1-866-881-2723
www.archdisabilitylaw.ca